# በሚሊኒየም ስም
# ሕዝባዊ ትግል አይገታም።

ኀጠኝነትን አጥብቄ እጠላለሁ። ዘረኛ አይደለሁም። ከመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በአንድነት መኖርን እወዳለሁ። የእናንተን አላውቅም። እኔ የሀገሬ ነገር ሞቴ ነው። አገሬ ክብሬ ነች። መመኪያዬ ነች። ኩራቴ ነች። ኢትዮጵያ የሕይወት እስትንፋሴ ነች። በዘር የተሳሰረ፣ በታሪክ የተጣመረ፣ በባሕል የከበረ፣ በእምነት የተቆረኜ አስተዋይና ጀግና ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አይ መስለኝም።

ቃል ኪዳን ነውና የሀገር ትዝታ በሕልምም በእውንም በቅዥት መልክም ይታያል። አያድርስነው። ስንከሳር ነው። ተጽፎም ተነቦም አያልቅም። ወደ ስማይ ሲውጡ፣ እንጦረጦስ ሲወርዱ፣ሲጋልቡ፣ ሲሸከረከሩ፣ ሲዋኙ፣ በደረቅ ሌሊት ሲባክኑ ማደር። ለማይጨበጥ፥ለማይዳሰስነገር በከንቱ መዳከር። ጭንቅላት ያጠነጠነውን ክር ሲፈቱ ሲቋጥሩ መኖር፥ ሳቁ፣ጨዋታው፣ቀልዱ፣ ቁምነገሩ ሁሉ የሚያምር በሀገር ላይ ነበር።

የሕልም እንጀራ ሥሥት፣ ዘወትር የሐሳብ ምርኮኛ፤ የማያልቀውን መንገድ መወጠን፤ የማይፈጸመውን ዓላማ መትለም፤ የሩቁን በቅርብ መመልከት፤ የቅርቡን እያዩ መሸሽ፤ ዘወትር የነገር ቡትቱ መደረት፤ ትልቅ ሸክም ማንሳት መጣል፤ ስለሀገር፥ ስለወገን እያወሱ መትከንከን መርመጥመጥ።

መቼ ነው ከዚህ ሁሉ የኀሊና ሸክም የምንገላገለው? መቼ ነው ችግሮቻችንን በመቻቻል በመከባበር የምንቀረፈው? እውን ይህ ትውልድ የተረገመ ነውን? ወይስ የሰቆቃው መፍቻ ቁልፍ ጠፍቶ ሊቀር ነው? ኀበዝ ሞተን ሳናልቅ ፍቱን መድኃኒት በጋራ እንፈልግ። የታሪክ አደራና የዜግነት ኃላፊነት ያለብን ይመስለኛል።

እስቲ ለአንድ አፍታ የኢትዮጵያን ካርታ እንመልከት። ራሷን ቆርጠው ሲጥሏት ስናይ ኀሊናን አይዘገንንምን? እግሮቿን ዘርጥጠው ሊጥሏት አስፍሰፈዋል። ነፍጥ ደቅነዋል። ደም ለማፍሰስ፥ ሀገርን ለመቁረስና ለመበታተን ድግሱ ቀጥሏል። እርዳታውም ይጎርፋል። አስጊ ነው። በዋዛ አይታ ይም። መወያየት መነጋገር መፍትሄ መፈለግ አሁን ነው። ሁለንተናዋን እየቦረቦሩ ተቀራምተዋታል። ማሩ ተቆርጦ ተሸኝቷል። ንቢቱም ትበራለች። ሸዕቢያ ሰባት(7) ዓመት ዘረፈ። ወያኔ ዐሥራ ሰባት (17) ዓመት ሳሚን አለበ። እንደመዥገር ተጣብቆ ጋጠ። ገና አልጠገበም። ሆዳም ነው።

ወያኔ ሀገሩን የማይወድ አረመኔ ባንዳ ነው። የታሪካዊ ጠላቶቻችን የባዕዳን አሻንጉሊት ነው። ታሪኳን ያረከሰ፥ ባንዴራዋን ያንኳሰሰ ዝቃጭ አተላ ነው። ማፈሪያ ነው፤ የወያኔ ሎሌዎችና ደጋፊዎች ልታፍሩና ልትሸማቀቁ ይገባል። ወያኔ የእንግዴ ልጅ ነውና።

በሚሊኒየም ስም ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ሽር ጉድ ያበዛችሁ ራሳችሁን መርምሩ? በሕዝብ ስቃይና መከራ ላይ ለመጨፈር? ወይስ የወያኔ አለቅላቂና አጨብጫቢ ለመሆን? ባትፈጠሩ ወይም ተጨንገፋችሁ ብትቀሩ ይሻል ነበር። አዲስ አበባ በእያንዳንዱ ፎቅላይ መትረየስ ተጠምዶ ፤ በየቦታው ነጭ ለባሽ ተስግስጎ፤ በሄድክበት ሁሉ ጆሮ ጠቢ እየተከታተለህ ምን ዓይነት በዓል ልታከብር ተፈልጋለህ? አለመታደል ሆነና ያቺ ጥንታዊትና ታሪካዊት እናት ሀገር ነጻነት የራቃት፤ የቀን ጨለማ የዋጣት ሆነች። ኢትዮጵያ ሄዳችሁ ከላይ ብትወጡ ወያኔ፣ ከታች ብትወርዱ ወያኔ፣ በዚህም ወያኔ፣ በዚያም ወያኔ፣ የት ይደርሳል። መውጫ መግቢያው «አጋአዚ ጦር» ነው።

ወያኔ የሒትለርን ዓርማ አንስቶ ሕዝብን በአደባባይ የጨፈጨፈ ፀረ-ሕዝብ ነው። አገርን አሳልፎ የሸጠ ከሐዲ ነው። በውሸት የነገሠ ቀጣፊ ነው። በወያኔ ጥይት የረገፈው የሕዝብ ደም አሁንም ይጮሃል!! በሕዝብ ከፍተኛ ድምጽ ድልን የተጎናጸፉት የኢትዮጵያ መሪዎች የሀገር አልኝታዎች ወሕኒ ቤት ታጉረዋል። አሁን ደግሞ ይባስ ተብሎ የሞት ፍርድ ሊያስበይንባቸው እየተዘጋጀ ነው።

አንተና አንቺ «በሚሊኒየም ስም»!! አገር ቤት ሄዳችሁ የወያኔን ዝግጅት ለማድመቅ አስባችሁ ከሆነ የፕሮፌሰር አስራት አጥንት ይወጋችኋል። የአሰፋ ማሩ ደም ይረጫችኋል። እስር ቤት የሚማቅቀው ወገናችሁ ይታዘባችኋል። በበሽታ የሚረግፈው ጎስቋላ ሕዝብ ያዝንባችኋል። በወያኔ ፖሊስ አፈሙዝ ተደቅኖበት መንቀሳቀሻ ያጣው ወንድማችሁ ያለቅስባችኋል።

ሕዝብ በርሀብ አለንጋ እየተሸነቆጠ፤ ድሃ የሚበላው አጥቶ ጦሙን እያደረ፣ ወገን በተላላፊ በሽታ እንደ ቅጠል እየረገፈ እናንተ ከጭራቁ ከመለሰ ጋር የዊስኪ ብርጭቆ ጨብጣችሁ ልትዘፍኑ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋረዳችኋል።

ወያኔ ብቻውን ከበሮ እየደለቀ ይጨፍር። መቼም አዙሮ የሚያይበት አንገት አልተሠራለትም። የሕ ዝብን ከበሬታ ያጣ ሕዝባዊ መሠረት የሌለው በአየር ላይ ተንሳፎ የሚንገዋለል የተነፋ ባሉን ነው። አንድ ቀን ይተነፍሳል።

ስለዚህ እንዳንተዛዘብ አርፋችሁ ተቀመጡ። በስደተኛነት ወግና ደንብ ተከባብረን፣ ተቀራርበን ዋሽንግተን ዲ. ሲ. በሚከበረው **«የሚሊኒየም በዓል ዝግጅት»** ላይ ተገኝተን ድኃ ወገኖቻችንን እያሰብን አስተዋጽኦ እናበርክት።

ዘወርቅ መንበሩ
ከቴክሳስ